# አደገኛና የተቀነባበረ ሀገር የማፍረስ ሤራ

## ሀገርን ላለመነጠቅ በመልካም ፈቃድም ላለመጥፋት የተደገሰልንን የጥፋት ዘመቻ እንቋቋም

ሀገራችንን ለማፍረስ ዘራችንንም ለማቀጨጭና ለማጥፋት፣ ባህልና ታሪካዊ እሴቶች እንዲወድሙና ኩራትና ክብራችንን ያጣን ሆነን እንድንበተን ከፍተኛ ድግስ ተደግሶልናል። የሀገር ጉዳይ ያገባናል ብላችሁ ተደራጅታችሁ ነገር ግን ትኩረታችሁ ሌሎች ተቃዋሚዎችን መተቸትና በተናጠል መታገል የሆነው ተነጣጥላችሁ ወደ እርድ ከመሄድ ይልቅ ወደ አንድነት በሚወስደው ጎዳና ለመገስገስ ፍጠኑ።

ብሄራዊ አንድነትን አስቀድማችሁ በጋራ ለመስራት የወሰናችሁም የጀመራችሁትን የዓላማና የተግባር አንድነት አጠናክራችሁ ግፋበት። ፖለቲካ አያገባኝም የምትሉና የሌላው ቤት ፈርሶ፣ አካልና ህይወቱንም መስዋዕት አድርጎ በሚያስገኘው ነፃነት የተደላደለ ህይወት መኖር የምትሹ ወይ ከዚህ ቅዠት ቶሎ ንቁ አለዚያም ከተቆፈረላችሁ ጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ለመግባት ዝግጅታችሁን አጠናክሩ። ፖለቲካውን ለመተዳደርያ ይዛችሁ ከመለስ ወንበር በቀኝም ይሁን በግራው የቆማችሁ በወያኔ ማፍያዎች መበላታችሁ እርግጥ ነውና ወደ ህሊናችሁ ተመልሳችሁ ለሀቅ መታገል ምርጫችሁ ይሁን። ይህን ማድረግ ካልቻላችሁ 'በሬ ሆይ ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ እልም ካለው ገደል ገብተህ ቀረህ ወይ' እየተባለ መተረቻና መዛበቻ ትሆናላችሁ። ከዚያም በላይ ደግሞ በወንጀልም ተጠያቂ መሆናችሁን አትዘንጉ።

መንገድ ሁሉ በእግዚአብሄር ነው እየተባላችሁ ጠላት በፀሎት ብቻ ልታንበረክኩ የተጋችሁ ሕዝበ ክርስቲያኖች ቤተክርስትያናችሁ በባንዳ ጳጳስ፣ ቤተመቅደሳችሁ በታጠቁ ሰላዮች እየታገተ ለጠላት እንድትገዙ በሚገዝቱ ቀሳውስት እጅ እየወደቀ መሆኑን አትደግፉምና ሃይማኖታችሁንም አገራችሁንም ለማዳን ተነሱ። ታላላቅ የቤተክህነት ሕንጻዎችን ተግተን ስንገነባ በረንዳ አዳሪዎችን፣ ረሀብተኞችን፣ ስራ አጦችን፣ ከመሬት ከንብረታቸው ተገፍተው ያሉ ከርታቶችን፣ በግፍ የሚታሰሩ፣ የሚቀጠቀጡና የሚገደሉ ወገኖችን እናስባቸው። የኢትዮጵያንና የሕዝቧን መዋረድም እንመልከት።

የተለያዩ ቤተክርስትያናት ተከታዮች የሆናችሁም በዘመነ ኮሎኒያሊዝም ጆሞ ኬንያታ "እኛ መፅሀፍ ቅዱስ ይዘን ሃሌሉያ ስንል ፈረንጆች አሜን እያሉ ሀገራችንን ነጠቁን" ያሉትን አይነት አገራችሁን በኢንቨስትመንት ስም የሕንድ፣ የአረብ፣ የኮርያ፣ የቻይናና የሌሎችም አገሮች ባለጠጎች እየተቀራመቱት መሆኑን ልብ በሉ። ልብ ብላችሁም ዝም አትበሉ። ሀይማኖት የፈለቀባቸው ሀገሮች ሀገራቸውን በደማቸው እየዋጁ በነፃነት አቆይተዋልና ሀገር እየሰጡ ሃሌሉያ ለፅድቅም አይሆንም!! የእምነት ቤቶች ለእውነት ለሚታገሉ፣ ለፍትህ ለሚቆሙ፣ ለነፃነት ለሚሰለፉ እንጂ የፈሪዎች ምሽግ፣ የአድር ባዮች ከለላ ሊሆን አይገባም።

የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችም እንዲሁ በሀገራችሁ ላይ እየተፈጠረ ያለውን ደባ በአግባቡ መርምራችሁ በሀይማኖት ጣልቃ እየገባ የራሱን ተላላኪዎች በማስረግ አብራችሁ በኖራችሁት ክርስትያን ላይ እንድታኮርፉ እየገፋፋ ግን ቆንጨራ በአናታችሁ ላይ ለማሳረፍ በተጠንቀቅ የቆመውን አገር አጥፊ የማፍያ ቡድን አትርሱ። ከክርስትያን ወንድም እህቶቻችሁ ጋር በመሆን ፊታችሁን የጋራ ጠላታችሁ ወደሆነው ወያኔ አዙሩ።

ሃይማኖት ከሀገርም፣ ከባህልም፣ ከነፃነትም በላይ ነው ብላችሁ በምድር የሚያኖራችሁን የሕልውናችሁ መገለጫ የሆነውን ማንነት በመሰሪዎች አታስነጥቁ። ከአንገታችሁ ቀና አድርጎ የሚያስኬዳችሁ ቀደምት ኢትዮጵያውያን በደማቸው በዋጁት ነፃነት እንዲሁም ባቆዩላችሁ አገርና ባሕል ነውና በናንተ ዘመን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እንዲጠፋ አታድርጉ። ከቤተመቅደስ ፅላት ከቤተ መዘክር የድንቅነሽን አፅም ሳይቀር አውጥተው የሸጡ ያገር ጠላቶችን መታገል፣ መሞገትና ሌቦችን፣ ገዳዮችን ከስልጣን ማስወገድ በእግዜርም ዘንድ የሚያስከብር መሆኑ ከናንተ የተሰወረ ሊሆን አይችልም።

በሀገር መከላከያ ስም የትግራይ ተገንጣይ ቡድን ሰራዊት ሆናችሁ እነ መለስ ዜናዊ ሲሻቸው በኮንትራት ሲፈልጉም ለውጭ ሀገር መንግስታት በተላላኪነት በናንተ ሕይወት ላይ እንዳሻቸው እንዲያዙበት አትፍቀዱላቸው። ወገኖቻችሁን ከመሬታቸው እየነቀሉ ለባዕድ ለሚሸጡ ከሀዲዎች አድራችሁ ጎስቋላና ድሀ ወገኖቻችሁን አትጨፍጭፉ።

ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በጋራ ማዳን ካልቻልን በተናጠል ልንጠፋ የግድ ነውና ፈጥነን እጅ ለእጅ እንያያዝ። የማንነታችሁ መገለጫና የክብር ዓርማችሁ ኢትዮጵያ ተሸራርፋ በጨረታ እየተሸጠች ነውና ዳር የቆማችሁ ምሁራን ወደ መሀል ግቡ። የናንተም ይሁኑ የሌላ ወገኖቻችሁ ልጆች ተስፋ ቢስ እንዲሆኑ እንደናንተው ተምረው ለሀገር ለዐለምም

የሚጠቅሙ እንዳይሆኑ ሲደረጉ አያገባንም ብትሉ፤ ትምህርት ቤቶች እውቀት አልባ ሰዎችን የሚያመርቱ የአደገኛ እጾችና የአልኮል መጠጥ ሱሰኞች እንዲሆኑ ሆን ብሎ የሚሰራውን የተነጣጠረ በደል አይቶ እንዳላየ ብታልፉት የህሊና ባለዕዳ መሆናችሁ አይቀርም። የስልጣኔ ፋና ያላዩ ሁዋላ ቀር እንደተባሉና አናሳ ተብለው እንደተመነዘሩ ዛሬ ደግሞ ከመሬታቸው እየተነቀሉ በግድ ወደ ማጎርያ (ሰፈራ) እየተነዱ ያሉትን ወገኖች አስቡ። ወትሮ ሰፈራ ሌሎች ኢትዮጵያውያንን ከተጎዳ መሬት ወደ ለም መሬት ማሸጋሸግ ነበር። የአሁኑ ሰፈራ ግን መሬታቸውን ለባዕዳን ለመሸጥ ሞታቸውን ወደሚጠብቁበት ሰፈራ የመውሰድ ፋሺስታዊ እርምጃ ነው። ኢትዮጵያችን ኢትዮጵያን አጥብቀው በሚጠሉ እንድትጠፋም በሚተጉ መሰሪዎች እየተዋረደች ነው። የነፃነት ትግል የአቅምና የድርሻ ይከፈልበታል እንጂ ለማንም በውክልና አይሰጥምና ሌሎች ታግለው ሀገር እንዲያቆዩልን መጠበቅ ከንቱ ምኞት ነው። ፈጥነን ካልተነሳን ሮጠንም ጥፋቱን ማቆም ከማንችልበት እንደርሳለንና አገር የማዳን ጊዜው አሁን ነው።

ቤት ንብረት አፍርተናል፣ ኢንቨስትመንት አለን የምትሉ በጠራራ ጸሀይ እየተነጠቃችሁ መሆኑን ከናንተ በላይ የሚያውቅ የለም። ፕሮጀክት ይዘን ለልማት ወደ ሀገራችን ገባን የምትሉ የድካማችሁን ውጤት ተነጥቃችሁ የናንተን ፕሮጀክቶች ወያኔዎች እየከበሩበት መሆኑም ድብቅ አይደለም። ዋስትና ለሌለው ንብረት ብላችሁ ራሳችሁን ከነፃነት ትግል ስታገልሉ በ አንድ በኩል የሕዝቡ ጥላቻ በሌላ በኩል የወያኔ መጫወቻ መሆን ትርፋችሁ ሊሆን አይገባም። ሕግ የሌለበት የምትገነቡት በሙሉ የአሸዋ ላይ ቤት ነው። ገንዘቡም መቆምያ በሌለው ግሸበት ገለባ እየሆነ ነው።

በዘርና በመንደር ተከፋፍላችሁ የወያኔን እድሜ አታራዝሙ። ምክንያቱም ወያኔ ለማንም አይመለስም። የትግራይ ሕዝብ የመከራው ገፈት ቀማሹ ነው። ክፉኛ ተቀጥቅጦአል በእቅፉ ያቆያቸው አንሶ በአውሮፕላን እያስጨፈጨፋት ፊልም ሲቀርፁ ኖረዋል። እየተዳሩ ያስረገዙዋቸውን ወይዛዝርት እየገደሉ ጉድጓድ የሚጥሉ አረመኔዎች ናቸው። አሁንም ይህንኑ ሕዝብ በጉያው ተወሽቀው ከቀሪው ወገኑ ጋር ጥርስ እያናከሱት ነው። አማራውን እየቀጠቀጡ ኦሮሞውን መግቢያ መውጫ አሳጥተው በየመንደሩ እየጨፈጨፉና በየእስርቤቱ እያጎሩ ነው። በደቡብ ሕዝቦች ላይ የሚደርሰውም ግፍ ከልክ ያለፈ ሆኖ የድህው ደም በየጉድባው እየፈሰሰ ነው። በኦሞ ሸለቆ ያለው ዘግናኝ ሁኔታ እንቅልፍ ሊነሳን ይገባል። በአኝዋክ ሕዝብ ላይ የሚደረገው የዘር ማጥፋት፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ የሚደረገው ማፈናቀል ነገ የሌሎች ኢትዮጵያውያንም እድል ምን ሊሆን እንደሚችል አመላካች ነው። ያልተነካ ወገን ያልተበደለ ጎሳ የለምና የመነሳት ጊዜ አሁን ነው። ጥፋት እየተነጣጠረ ያለው በአንድ ወይም በሁለት ጎሳ፣ ዘር፣ ጎጥ አይደለም ለሁሉም በየተራ የሚዳረስ የክፋትና የጥላቻ መርዝ እንጂ። ሕዝቡ እንዲህ እየተዋረደ የቁም ሞት እየሞተ ሰላማዊ እንቅልፍ እንደምን ይተኛል? እስከ መቼስ ዝም ይባላል? ለምንስ በወገን ላይ የሚደርስ ቅጥ ያጣ ግፍ እንደዋዛ ይታያል? ለመሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ከባንዳዎቹ በቀር ከበደል ነፃ ነኝ የሚል ማን ነው? ባርነት እስከመቼ? ውርደትስ እስከመቼ?

አሁን ጊዜው ቆይ ነገ የሚባልበት ሳይሆን ተባብሮ ሆ ብሎ የሚነሱበት ወቅት ነው!! ወቅቱም የአሸናፊነት ነው!! የተዋረደች ሀገር ስትኖረን የሚያዋርደንና የሚያሳንሰንም ይበዛል። ለዚህም ስደተኛ እጅ ይዘው የሚያስረክቡ የጎረቤት ሀገራትን፣ የአረብ አገሮች የሚሰሩት ግፍንና አሁን ደግሞ በኖርዌይ እየሆነ ካለው ሁኔታ ልንማር ይገባል። ስደት ግማሽ ሞት እንጂ ነፃነት አይደለም።

በኢትዮጵያ እየሆነ ያለውን ሁኔታ እየተከታተሉ የሚገኙ የውጭ ሀገር ሰዎችና ድርጅቶች ኢትዮጵያውያን የማይፈልጉትን ነጻነት እኛ ምን ልናደርግ እንችላለን? በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ናቸው የሚንቀሳቀሱት። እንዴት በወያኔ ታሰርኩ፣ ተገረፍኩ፣ ከስራ ተባረርኩ እያሉ ጥገኝነት የሚያገኙ ሰዎች የሀገሪቱ መፍረስ አይታያቸውም? የችግሩ ክብደት አይታያቸውም? እያሉ ሲጠይቁ እውነትም ኢትዮጵያ እንደ አሮጌ ቁና ብጥስጥሷ ቢወጣም የራሳቸውን ኑሮ የሚኖሩ ግድ የላቸውም ቢሉ እንደምን ይፈረዳል? አረ የመገፋት ቁጣ ይቀስቅሰን!! አረ የወገን ሰቆቃ ከተኛንበት ያንቃን!! ለሕዝባችን ነፃነት ብለው የሞቱት ወገኖቻችን ደም ይጥራን!! አረ ቤተሰቦቻቸውን በትነው ወጣትነታቸውን ተነጥቀው በየእስር ቤቱ ያሉ ወንድም እህቶቻችን ስቃይ ያናግረን!! አረ ተከብራ የኖረች ኢትዮጵያ መፈራረስና የሕዝቡ መገፋት ያስተባብረን!!

ለኢትዮጵያ ጠላቶች በሚገባ እየሰራ ያለውን የሀገር ማጥፋት ሴራ ለማስታወስ በተከታታይ ጽሁፎችን እንደማቀርብ ቃል ልግባና የተነሱ እንነሳ ጥሪዬን በዚህ ላብቃ።

ዳኛቸው ቢያድግልኝ

biyadegelgne@hotmail.com